አውራምባ ታይምስ

በዳዊት አሳታሚ ድርጅት የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ
ዳዊት ከበደ

ም/ዋና አዘጋጅ
ወንድራድ ደብረጽዮን

ከፍተኛ አዘጋጅ
ፍፁም ማሞ

ሪፖርተር
አስራኤል ደርቤ

አምደኛ
ነበበ ብሩ

ዌብ ሳይት ኤዲተር
አብይ ሀብተማሪያም

ማርኬቲንግ ማናጀር
የኃላሸት አራጋው

ሴልስ
ሀብተ መስቀን

ሌይአውት ዲዛይነር
ነብዩ መስፍን
e-mail
nebiyou1st@yahoo.com

ኮምፒውተር ፅሁፍ
ፈቨን አወቀ

የዝንጅት ክፍሉ አድራሻ፡-

ካዛንቺስ ከቶታል ወደ ኡራኤል በሚወስደው መንገድ ከኪራይ ቤቶችአጀንሲ ፊት ለፊት ከአልሚታ ጀርባ
0911-629278
0911-629282
0911-877240
0911-366230
ፖ.ሣ.ቁ 19325
አዲስ አበባ

e-mail
AwrambaTimes@gmail.com

ርዕሰ አንቀፅ

በንቅናቄው ዙሪያ የምንለውን ለማለት ወደድን!

በበርካታ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ በሰላማዊ ትግል አርበኝነታቸው የሚታወቁት ዶ/ር ብረሃኑ ነጋ ከኢጋሮቻቸው ጋር በመሆን አመፅን ማፅከል ያደረገ የትግል ስልት መምረጣቸውን በይፋ አውጀዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች አመፅን መሰረት ያደረገ የትግል ስልት መምረጣቸው ዝግጅት ክፍላችንን ከማስደንገጥ አልፎ እየሆነ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ መልኩን እንዲቀይርም ባለድርሻ አካላትም የየራሳቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለባቸው እና ዜጎች የማወቅ መብት እንዳላቸው በማመን ይኸን ልዩ እትም (Special edition) ለአንባቢያን እንድትበቃ በተጀመረው ንቅናቄ ዙሪያ የምንለውን ለማለት ወደድን፡፡

ዶ/ር ብርሃኑም ሆኑ ሌሎች አጋሮቻቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያዊነት ባሻገር በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸው ዜጎችም ጭምር፡፡ ወደድንም ጠላን የእነዚህ ሰዎች አቋም የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎት ነፀብራቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ሁሉ መነሻቸው የህብረተሰቡ ፍላጎት፣ እምነት እና የሚፈጠሩ አጋጣሚዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ዜጎች የመረጡትን የትግል ስልት ስንኮነን በእነሱ አስተሳሰብ የሚያምኑ ሌሎች ዜጎችንም መጫን ነው፡፡ አንደ ሚዲያ ተቋም የተለያዩ የትግል ስልት መርህን ለመከተል የፖለቲካ መድረኩን ለተቀላቀሉ ወገኖች ሃሳባቸውን በነፃነት እና በይፋ እንዲገልፁ ማበረታታት የሞያው ሃላፊነት ነው፡፡ አርግጥ ይህንን ስናደርግ በሃገሪቱ ውስጥ በየደረጃው ያሉ ህጎች መአቀፍ ውስጥ ሆነን መሆን እንዳለበት ከግምት ውስጥ በመክተት ነው፡፡ ሕገ መንግስታችን በአመፅ የተመሰረተ የፖለቲካ ትግልን አይፈቅድም፡፡ ይህ ማለት ግን በነፃነት እጦት ስቃይ ውስጥ ያለ ሰው ቢያምፅ በሞራላዊ መመዘኛ ትክክል አይደለም ብሎ ማለት ተገቢ አካሄድ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱን አካሄድ «የተነጠቀን መብት ለማስመለስ» የሚደረግ ከሆነ ተገቢ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ እንዳንዶች በነሲብ ለሚያራምዱት እምነት በቂ የሃሳብ መንደርደሪያ ሲያቀርቡ ከድምጾሚ ላይ ደርሰው የሰዎችን ውሳኔ ማብጠልጠል እና ትክክል እንዳልሆኑ ለመናገር ይጓጓቸዋል፡፡ ወይም የዋሉበትን ለመምሰል አልያም ከመጠን በላይ በፍርሃት ተውጠው ለዴሞክራሲ ስርዓት እጦት ሌላ አማራጭን ይዘው የሚቀርቡ ሃይሎች የሚያመጡት አስተሳሰብ አልዋጥላችሁ ያላቸውም አሉ፡፡ እዚህ ላይ «ለምን ፈሩ? ለምን አነባቢያቸውን መሰሉ?» የሚል ጥያቄ ለማንሳት ፍላጎት የለንም፡፡ ነገር ግን እነዚህ የንቅናቄውን አጀንዳ ይዘው የተነሱ ሰዎች ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ወደ ቀብር እያንደረደረው ያለውን ሃይል ድርድር ውስጥ እንዲገባ እና የነፃነት የፍትህና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያ ምድር ማስፈንጋገብ አደርጎ የተነሳ ነው እያሉን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህንን ሃሳብ አንስተው መከራከሪያ ነጥባቸውን በአግባቡ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ተንትነው ሲያቀርቡ በተቃራኒው ያሉት ግን በምንም መመዘኛ ስፍራ የሚባታ አሳማኝ ምክንያት አቅርበው ስለ ምን ሰላማዊ ትግል እንደሚያደርጉ የመከራከሪያ ሃሳብ አያቀርቡም፡፡ ቢያቀርቡም እዚህ ግባ የሚባል አሳማኝ መከራከሪያ አይደለም፡፡ የንቅናቄው አባላት አሳማኝ የሚሉትን መከራከሪያ ከማቅረብ አልፈው ወደ ትንታኔ ባመሩበት ሁኔታ ሌሎቹ ሃይሎች ግን ዝም ብሎ አይሆንምና አትንኩን በማለት ብቻ የአምባገነን ስርዓት አስተሳሰብ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲተገብሩ ይስተዋላል፡፡ እሁን በአገራችን ያለው የሰላማዊ ትግል ሜዳ እውነቱን ለመናገር ለአስመሳይ ፖለቲከኞች እንኳን የሚመች ሁኔታ አይደለም፡፡ ይህንን መንግስት ራሱ ሳያውቅ የሚቀር አይመስለንም፡፡ ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ከምርጫው እራሳቸውን አግልለው በህይወት የሌለ ሰው ተወዳድሮ ምርጫ አሸንፏል እየተባለ ባለበት አገር ይህንን በዴሞክራሲ በፍትህ እና በነፃነት ላይ የዳመነው ጥቁር ዳመና እንዲቀልጥ ኘሬሱ እና ሌሎች አካላት ምን መደረግ አለበት? የሚለው የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ አለባቸው፡፡ እዚህ ጋር ሰከን ብለን የምናስብበት እንጂ ይህ አካሄድ ትክክል አይደለም ብሎ ዘራፍ ማለት አሁንም ተገቢ አይደለም፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ መንግስትም ሆነ ሌሎች የተለያየ የፖለቲካ ጥያቄ ያላቸው ሰዎች ለሁላችን የምትበጅ የወደፊትዋ ኢትዮጵያ ለመፍጠር መሪ የሚያስተክሉበት አጋጣሚ መፍጠር እንዳለባቸው ጥቆማ የሚሰጡ ክስተቶች እየተስተዋሉ ነው፡፡ ሁሉም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሰላማዊ ገፅታ እንዲኖረው በፖለቲካ መድረኩ ዙሪያ ሁሉን አቀፍ ስምምነት መደረግ ያለበት ይመስለናል፡፡ አንተ ትክክል ነህ አይደለህም ለማለት ማንኛውም አካል ምንም አይነት ማስረጃ የማቅረብ ብቃት ያለው አይመስለንም፡፡ በስሜት አንተ እንዲህ ነህ፡፡ እኔ እንዲህ ነኝ መባባሉ ስምኝኛ ዉልት ውስጥ መግባት እንጂ ጠቃሚ አይመስለንም፡፡ እነ ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ አይነት የትግል ስልት ለምን መረጡ? ይህ መመለስ ያለበት ይመስለናል፡፡ ምክንያቱም ስለ ሰላማዊ ትግል መስከረው የማይጠግቡት እኝህ ሰው ይህንን ንቅናቄ የአመፅ ባህሪ እንዲይዝ መምረጣቸው በጣም የተገላበጠ አቋም ነው፡፡ ማሰብ የሚችል ሰው የእኝህ ሰው አቋም ፈረንጆች U-turn እንደሚሉት በአንድ ጊዜ መቀየሩ ያለ ምክንያት እንዳልሆነ መገመት አያችትም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ከጊዜበት የትግል ምዕራፍ እንዲመለሱ ከመፀለይ ባሻገር መሰራት ያለባቸው መሰረታዊ መርሆች እንዳሉ መገንዘብ አለብን፡፡ መንግስት የሰላማዊ ትግል መንገዶች እንዲመቻቹ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ተሰፋ መቁረጥ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲነግስ ከተፈቀደለት እንዲነቃነቅ የማንፈልገው ነገር መነቃነቁ እይቀሬ ነው፡፡ መንግስት በተለያዩ መመዘኛዎች ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲጎለብት በማድረግ ረገድ ፈተናዎችን እየወደቀ ነው፡፡ ወደ ፖርላማ ለመፅደቅ የተንደረደረው የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት ረቂቅ ህግ ቢፀድቅ የሚኖረው ሃሳብን የመግለፅ መብት በሚገርም ማነቆ ውስጥ የሚወድቅበት አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ይህ ደግሞ አንዱን እና በተለያዩ ሃገራት ከመኖር መብት ጋር በእኛነት የሚያዩትን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን ዲሞክራሲያዊ መብት ገድቦ ምን አይነት ሰላማዊ የትግል መንፈስ በኢትዮጵያ ለማስፈን እንደታቀደ አይገባንም፡፡ የሚገርመው ነገር ይህ ረቂቅ ለህገ መንግስቱም የማይመሰስ ረቂቅ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አመፅን መአከል ያደረገ የትግል ስልት ሀጋጭ መአቀፍ የለውም ብለናል፡፡ ይህንን የህግ ማዕቀፍ ግን ለመጠበቅ እና ለሁላችን የሆነችውን ኢትዮጵያ ከነልዩነታችን አቅፎ የሚሄድ ሂደት መፍጠር እና የትግል ስልቶቻችን ከቡራቡሬ መከመር እንዲላቀቅ ማድረግ ይናርብናል፡፡ ይህ ባይሆንስ? ብዙ የማንፈልጋቸው ችግሮች ይፈጠራሉ የአገር አንድነት ዋስትና ማጣት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት መነገስ ፣ተፋቅረን፣ ተዋደን የመኖር ተስፋ፣ የተረጋጋ የፖለቲካ ስብዕና እና መጨካከን በአገራችን እንዲነግስ እድል መስጠት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ገገርው ፖርቲም ቢሆን የሚፈልገው አይደለም፡፡ ምክንያቱም አመራር ላይ ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ የኢትዮጵያን ወደፊት ማበብን እና መበልፀግን የማይፈልጉ ዜጎች ናቸው ብለን መደምደም አንፈልግም፡፡ የእነሱ አስተሳሰብ በተግባር ላይ ውሎ ውጤታማ እንዲሆን ይፈልጉ ይሆናል እንጂ በአገራቸው ላይ የጠላትነት ድርሻ እንዲኖራቸው አይፈልጉም የሚል ከፍተኛ እምነት አለን፡፡ ስለዚህ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ወሳኝ የሆኑ የስራ ድራሻቸውን ዛሬ ነገ ሳይሉ አሁኑኑ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ሰዎች በሰላማዊ ትግል ተስፋ እንዳይቆርጡ እና ሌላ የትግል ስልቶችን እንዳይከተሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ሁሉም ተዋደን እና ተፋቅረን የምንኖርባት ኢትዮጵያን መፍጠር የመጀመሪያውን የቤት ስራ ልናደርገው ይገባል፡፡ በነገራችን ያለውን ሁሉን አቀፍ የሊሂቃን ተሳትፎ ማበራከት እና ስለ ሃገሬ ያገባኛል የሚሉትን ባለ ድርሻ አካላትን በየቀኑ የመፍጠር ብቃት የመንግስት የእለት ተእለት ስራ ሊሆን ይገባል፡፡ ከተቻለም ካሪፊ ሃይሎችም ጋር ቢሆን መወያየት እና መደጋገፍ ተገቢ ይመስለናል፡፡ ሁሌም ቢሆን ውሳኔዎችን ስንሰጥ መጤን ያለበት የማንኛውም ፖለቲከኛ አስተሳሰብ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍል አባላትን አስተሳሰብ ይወክላል ብሎ ማሰቡ ተገቢ ነው፡፡ ያን ጊዜ የሰዎችን አስተሳሰብ እናከብራለን፡፡ መፍትሄም እንሰጣለን ይህ ካልሆነ ግን አሁን የተፈጠረውን ቡራቡራ የአስተሳሰብ ሂደት በኢትዮጵያችን ውስጥ እንዳይሰፋፋ ስጋት አለን፡፡

አንባቢዎቻችን ስለዛሬው እትማችን ይዘት ምናልባት ጥያቄ ሊያጭርባችሁ ይችላል፡፡ እናም ስለዚች ልዩ እትም ማብራሪያ እንስጥ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጋዜጣችን በሀግ የበላይነት ታምናለች፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ህጎችን እናከብራለን፡፡ ጥሩም መጥፎም ህግ ቢሆን፣ ህግ ህግ ነውና፡፡ ምናልባት መጥፎዎቹን የምንላቸውን ህጎች መጥፎ ናቸው ብሎ መናገራችን እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ይህንን ልዩ እትም ስናዘጋጅ የዜጎች ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን መብት ሚዲያ ማክበር ስላለበት እና ዜጎች እየተፈጠረ ስላለው ነገር የማወቅ መብት ስላላቸው በሚል ነው፡፡ «የማንኛውም ሰው ሃሳብ የራሱ የሆነ ክብርም ሊኖረው ይገባል» በሚል ተነሳሽነት ነው እንጂ ጋዜጣችን ላይ ያሉት አስተሳሰቦች ሁሉ እናምንባቸዋለን ለማለት አይደለም፡፡ የኘሬስ ሞያዊ ስነምግባርም ይህንን አያስገድደንም፡፡

ሁላችንም አሳታፊ እና የምንወዳት ኢትዮጵያችን ለመገንባት እንታገል፡፡ ፖለቲከኞቻችን ልዩነታቸውን ለመፍታት ወኔያቸውን ሰብስበው እና ቀበቶአቸውን አጥብቀው ይንቀሳቀሱ፡፡ ሁሉንአቀፍ አሳታፊ ስርዓት እንዲፈጠር ሁላችንም የዜግነት ድርሻችንን እንወጣ፡፡ ፀሱት የሚያስፈልገው ጉዳይ ካለም እንደሰመድነው እጃችንን ወደ ፈጣሪ እዝርጋ!!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ሐምራዊ መፅሄት

ሐ

የፊታችን ቅዳሜ ይጠብቁት
አዝናኝ እና ቁም ነገር አዘል
ዘገባዎችን ይዘናል

ዝግጅት ክፍሉ

ሚያዚያ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ የሰርግ ስነስርአታችሁን በደመቀ ሁኔታ ያከበራችሁት

መልከጸዲቅ በቀለ
እና
ማህደር እሸቱ

ጋብቻችሁ የአብርሃምና የሳራ ይሆን ዘንድ መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን

ቤተሰቦቻችሁ ከአዲስ አበባ